## ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (ግንቦት 22 ቀን 2001 ዓ. ም.)

**የብአዴንና የመለስ ፍጥጫ እያየለ መሆኑ ነው፣ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ለግማሽ ሰዓት ያህል ቀይ ቆብ በደፉ ወታደሮች ታግተው  ዋሉ፣ ወያኔ ነባር ካድሬዎቹን እያነሳ አዲሶቹን እየተካ ነው፣ የወያኔው ነፍስ አባት ስልጣናቸውን ተነጠቁ፣ በሹም ሽሩ የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን እጁዋ አለበት >>>>>>>>>>**

**ከፍኖተ-ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ ......................**

ሲወራና ሲነገር የነበረው የመለስ እና የብአዴን ሽኩቻ ይፋ ወጥቶ ባለበት በአሁኑ ወቅት በብአዴን እና በመለስ መሀከል እጅግ ከፍተኛ ፍትጊያ ውስጥ  መሆናቸው ተነገረ።

ከዚህ ቀደም በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ የብአዴን ካድሬዎች የአንድ ሰው የበላይነት ሊወገድ ይገባዋል እያሉ ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያቀርቡ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት አጋጣሚውን ተጠቅመው እነ መለስ ዜናዊ እየለቀሙ በማሰራቸው የተነሳ በሌሎች ብአዴን  ካድሬዎች ዘንድ ከፍተኛ ቁጣ እየተቀሰቀሰ በመምጣቱ መለስ ዜናዊ እና በረከት ስምዖን ግራ ተጋብተው እንደሚገኙ ምንጮቹ አጋልጠዋል።

እጅግ ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ የገባው መለስ ዜናዊ ግንቦት 20 ቀን 2001 ዓ. ም. የ18ኛ ዓመታችን ነው ተብሎ በተከበረበት በዓል ላይ የወያኔ ባለስልጣናት ሲገኙ እሱ ግን በቤተመንግስት እንደነበረ ምንጮቹ ጠቁመው ይህ ሁሉ በውስጣቸው ያለው ክፍተትን አመላካች ነው ብለዋል።  በተለይ ግንቦት 19 ቀን 2001 ዓ.ም. መለስ ዜናዊ በቅርቡ ያቋቋቋማቸውና ያደራጃቸውን የሴቶች ማህበር፤የወጣቶች ማህበር እና ሌሎችንም በይፋ መመስረቱን ለማብሰርና እውቅና ተሰጠ ለማሰኘት በዝግጅቱ ላይ ለመገኘት ስድስት ኪሎ ከፍ ብሎ በሚገኘው የባህል አዳራሽ ደርሶ እስኪመለስ ድረስ እስከዛሬ ታይቶ በማይታውቅ ሁኔታ ከግማሽ ሰዓት በላይ ህዝቡ በፌዴራል ፖሊስ እና ቀይ ቆብ ባጠለቁ ወታደሮች ባሉበት ቦታ እንዳይንቀሳቀስ ተደርጎ እና ታግቶ የዋለ ሲሆን መለስም ያለ ወትሮው በስብሰባው ላይ ለጥቂት ደቂቃ ብቻ ቆይቶ መመለሱ በውስጡ ያለው ፍራቻን ግልጽ ያደረገ መሆኑንም ለመረዳት ተችሎዋል ሲሉ የቤተ መንግስት ምንጮች ገልጸዋል። በዕለቱ  በቦታው የነበሩ ሰዎች ባሉበት እንዲቆሙና ፊታቸውን ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ አዙረው እንዳይንቀሳቀሱ መደረጉም ታውቆዋል።

ዛሬ መለስ ዜናዊ ዙፋኔን ይነጥቁኛል በሚል እጅግ ወደር የሌለው ፍርሀት ውስጥ የገባው በብአዴኖች ላይ ባለው ጥርጣሬ ነው ያሉት ውስጥ አዋቂ ምንጮች በብአዴኖች ላይ ይህ ስጋት ሊያሳድር የቻለው ደግሞ ኢህአፓ ከጀርባቸው አለ ከሚል ጥርጣሬ የመነጨ መሆኑንም ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በሰራዊቱ ውስጥ ሲደረግ የነበረውን የብአዴን አባሎችን መመንጠሩ ለጊዜው ጋብ ያለ ሲሆን ይህም በቅርቡ የብአዴን ካድሬዎች ቁጣቸውን በማሰማታቸው መሆኑን የገለፀው ዘገባ በተለይ የብአዴን ካድሬዎች ብቻቸውን በየትም ቦታ እንዳይሰበሰቡ ከመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ እንደተሰጠም ዘገባው አጋልጦዋል።

የወያኔ ባለስልጣናት በተለይ መለስ ዜናዊና  በረከት ስምኦን የሚያደርጉት እና የሚይዙት ጠፍቶዋቸው ነባር ካድሬዎቹን ከነበሩበት ደረጃ ዝቅ እያደረጉ ምንም የማውቁትንና አዳዲስ ካድሬዎቹን ደግሞ ከፍተኛ ስልጣን እየሰጡዋቸው እርስ በርስ ትርምስ እየፈጠሩ መሆኑን እና በዚህም አለ በዚያ ችግር ውስጥ ወድቀው እንደሚገኙም ዘገባው አብራርቶዋል።

ይህ ሆኖ ባለበት በዚህ ወቅት መለስ ዜናዊ ሰሞኑን ስልጣን እንደሚለቅና ሌሎችም ነባር ከበረሀ የመጡ ባለስልጣናት ስልጣን ለአዲስ ተተኪ ወጣቶች ለመልቀቅ እንደሚገደዱ ገልጾዋል።መለስ ዜናዊ ስልጣናችንን መልቀቅ ጊዜው ግድ ይላል ብሎ መግለጫ በሰጠበት ሰሞን አዲስ የጡረታ ረቂቅ አውጥቶ ለተወካዮች ምክር ቤት ማቅረቡ ነገሮቹ እየተገጣጠሙ ስዕል ለመስራት እየተቃረቡ ናቸው ሲሉ በርካታ ምሁራኖች ሲገልጹ ተደምጠዋል።

መለስ ዜናዊን ጨምሮ ለአምስት ባለስልጣናት እያንዳንዳቸው አሁን የያዙት ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም ሳይቀር ወደፊትም በነሱ ቦታ ላይ የተቀመጠው ሰው እድገት ሲያገኝ  የእነሱም ደመወዝ አብሮ እንደሚያድግ የሚደነግግ ረቂቅ ቀርቦ ሰሞኑ የሚጸድቅ ሲሆን መለስ ዜናዊ በዚህ ወቅት ይህንን ለማድረግ ምን አነሳሳው ? ሲሉ የሚጠይቁ ብዙዎች ናቸው። አሁን በቀረበው ረቂቅ ላይ አምስት ባለስልጣናት ፕሬዝዳንቱ፤ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቱና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት ሲሆኑ እያንዳንዳቸው ከደመወዛቸው ውጭ ሶስት ሶስት ዘመናዊ መኪኖች ከነ ነዳጁ፤ ባለ አምስት መኝታ ክፍሎች ያሉት ቪላ ቤት እና ጥበቃዎች እንደሚመደቡላቸው ያዝዛል።

ወያኔ ነባር ካድሬዎቹን እያባረረና ከደረጃ ዝቅ እያደረገ ባለበት ወቅት አዳዲስ የተመለመሉትን ደግሞ ወደ የተለያዩ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ እያስገባ የካድሬነት ኮርስ እየሰጠ ሲሆን በቅርቡም ተመርቀው ወደ ስራ ይመደባሉ ተብሎ እየተጠበቀ  መሆኑ ተገለፀ።

በተለያዩ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ በሺህዎች የሚቆጠሩትን አዳዲስ ካድሬዎች እያሰለጠነ ሲሆን ተመርቀው ሲመጡ ነባሮቹን እንደሚተኩና ሙሉ ለሙሉ ስራውን እንደሚጀምሩ ተነግሮዋል። ነባር ካድሬዎቹና አዳዲስ ካድሬዎቹ በዚሁ ምክንያት እርስ በርስ ሽኩቻና ፀብ የፈጠሩ መሆኑም ታውቆዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ የሆነው ኩማ ደመቅሳ እንኩዋን ስልጣን ላይ ከወጣ በጣም አጭር ጊዜ ቢሆነውም ሰሞኑን ለሁለተኛ ጊዜ የመምሪያ ኃላፊዎችን ማባረሩንና በምትካቸው አዲስ ካድሬዎችን መተካቱ ታውቆዋል።

በወያኔው  የነፍስ አባት ኣባ ገ/መድህን  እና ለመለስ ዜናዊ ባለቤት የቅርብ ዘመድ ናቸው የተባሉት አቡነ ሳሙኤል መሀከል የተጀመረው ንትርክ ወደ ስድብ ማደጉን ከውስጥ አዋቂዎች የደረሰን ዘገባ ገለፀ:: ባለፈው ሳምንት ውስጥ ሁለቱ ጳጳሳት ከእምነት አባቶች የማይጠበቅ ስድብ እርስ በርስ ሲሞሻለቁ የተደመጠ ሲሆን በሁለቱ ጳጳሳት መሀከል ሌሎች ጳጳሶች ተገኝተው አንተም ተው አንተም ተው ቢሉም ሰሚና አድማጭ አጥተው ሲሰዳደቡ እንዳረፈዱ ታውቆአል::

ሁለቱም የወያኔን ትግል በበረሀ እና በከተማ ውስጥ ሆነው ሲደግፉና ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ ሲያደርጉ እንደነበረ የገለፁት ምንጮች በተለይ ኣባ ገ/መድህን ከአሜሪካ ህዝበ ክርስቲያን ለቤተክርስቲያን የሚሰጠውን ገንዘብ እየሰበሰቡ ለወያኔ ስንቅና ትጥቅ መግዣ እየላኩ ብርቱ ድጋፍ ሲያደርጉ በመቆየታቸው ላደረጉት ውለታ ከቤተክርስቲያኑዋ ቀኖና እና ህግ ውጭ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ተደርገው የተሾሙ ሲሆን መንበረ ስልጣኑን ከተቆጣጠሩበት ዕለት ጀምሮ እስከ ባለፈው ሳምንት ድረስ ለ18 ዓመታት የህዝበ ክርስቲያን ሀብት እየመዘበሩ ለግል ጥቅማቸውና ለወያኔ አፋኝ ስርዓት ድጋፍ ሲያደርጉ የቆዩ መሆኑን እና በአሁኑ ሰዓት ግን ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ ስልጣናቸውን መነጠቃቸውን ምንጮቹ አጋልጠዋል::

በተለይ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ አምባገነኑ የደርግ መሪ መንግስቱ ኃይለማሪያም በየአደባባዩ ምስሉን እንዳስለጠፈው ሁሉ የወያኔው ነፍስ አባት  እንደ ካድሬ ምስላቸውን በማስለጠፋቸው እና በህዝበ ክርስቲያኑ ገንዘብ ሲጫወቱበት ጥቂት ለእምነታቸው ያደሩ ለቤተክርስቲያኑዋ ህግ የተገዙ ጳጳሳት ድርጊቱን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ ሲቃወሙና ለሰውዬው ምክርና ተግሳፅ ቢሰጡዋቸውም አሻፈረኝ ያሉት ኣባ ገ/መድህን ከግንቦት 13 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ በመንፈሳዊ ሰበካና ግልጋሎት ብቻ ተወስነው ሌላውን አስተዳደራዊም ሆነ ገንዘብ ነክ ስራዎቹን ተነጥቀው ለተመረጡ ሰባት ጳጳሳት ማስረከባቸው ታውቆዋል:: 43 ጳጳሳት ለ8 ተከታታይ ቀናት እንደ ወያኔ ድርጅቶችና ተለጣፊዎች ሁሉ ግምገማ ከደረጉ በሁዋላ ኣባ ገ/መድህን ለጊዜው በመንፈሳዊ ስራ ላይ ብቻ እንዲቆዩና ሌላውን ስልጣናቸውን ግን ሙሉ ለሙሉ ለተመረጠው ኮሚቴ እንዲያስረክቡ መደረጉን ለማወቅ ችለናል::

አቡነ ሳሙኤል በበኩላቸው ወያኔ በረሀ እያለ በዋልድባ ገዳም እና በሌሎችም አካባቢዎች እየዞሩ ቤተክርስቲያናት ልናሰራ ነው በማለት  ከህዝበ ክርስቲያን  ላይ እያታለሉ የሰበሰቡትን ገንዘብ ለጦር መሳሪያ መግዣ እና ለስንቅ ድጋፍ ሲያደርጉ የነበረ ሲሆን ወያኔ አዲስ አበባን ሲቆጣር የጵጵስና ማዕረግ እንዲያገኙ የተደረገና በአሁኑ ሰዓት የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ  ሆነው የተሾሙ መሆኑን የምንጮቹ ጥቆማ ያስረዳል:: ሁለቱም ታጋይ ጳጳሳት ለወያኔ በየበኩላቸው ከፍተኛ ድጋፍ ሲያደርጉ እንደነበርና ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ግን በጥቅምና በስልጣን ጉዳይ ላይ ባለመግባባታቸው ምክንያት ፀቡ ሊፈጠር እንደቻለ  አጋልጠዋል:: ታዛቢዎች የወያኔ መሪዎች በሚገርም እና በሚደንቅ ሁኔታ ውስጣዊ ሽኩቻቸው እያየለ ባለበት በዚህ ወቅት እነዚህም መንፈሳዊ አባት ተብዬዎች መሀከል ሁኔታው መፈጠሩ አያስደንቅም ይላሉ:: የመለስ ባለቤት አዜብ መስፍን ኣባ ገ/መድህንን  እየጎነተለች እረፍት ስታሳጣ እንደነበረና አሁን የያዙትን ስልጣን እንዲነጠቁም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳበረከተች መንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

ለጊዜው ለአንድ ዓመት ስራውን ሙሉ ለሙሉ የሚሰራና በበላይነት የሚቆጣጠር ሰባት ጳጳሳት ያሉበት አንድ ኮሚቴ የተቋዋቋዋመ ሲሆን በዚህ ኮሚቴ ውስጥ የተመረጡት አቡነ ሳሙኤል ፤አቡነ አትናቲዎስ፤ አቡነ እስጢፋኖስ፤ አቡነ ጎርጎርዮስ ፤አቡነ ፋኑኤል፤ አቡነ መልከ ፀዲቅ እና አቡነ ጢሞቲዊስ የተባሉት መሆናቸውም ታውቆዋል፡፡

ከስልጣናቸው መነጠቅ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ኣባ ገ/መድህን 18 አዲስ ጳጳሳትን ለመሾምና ደጋፊ ለማድረግ እጩዎቹን አቅርበው የነበረ ቢሆንም የተሰበሰቡት 43 ጳጳሳት ሹመቱን በሙሉ ድምፅ ውድቅ አድርገውታል፡፡